# የአሌክሳንድሪያ ከተማ ለ South Pickett Street ኮሪደር ፕሮጀክት የማህበረሰብ ግብዓት ለማግኘት ይፈልጋል

የአሌክሳንድሪያ ከተማ ስለ South Pickett Street የትራንስፖርት ፍላጎቶች እና ተግዳሮቶች ላይ የማህበረሰብ ግብዓት ለማግኘት ይፈልጋል። ይህ በ Duke Street እና Edsall Road መካከል ያለውን የ South Pickett Street ኮሪደርን የሚጠቀሙ የሁሉንም የመንገድ መጓጓዣ አይነቶች፣ በሁሉም የእድሜ ደረጃዎችና ችሎታዎች ላይ የሚገኙ ሰዎችን እንቅስቃሴ፣ ተደራሽነት እና ደህንነት ለማሻሻል የተያዘው የከተማው የ South Pickett Street Corridor Improvements Project ኮሪደር የማሻሻያ ፕሮጀክቶች አካል ነው።

**እስከ ታህሳስ 22 የኦንላይን የግብረ መልስ ቅጽ ይሙሉ።**

ከተማው ከዚህ የመጀመሪያ የማህበረሰብ አስተያየት ጊዜ በሚያገኘው ግብረ መልስ፣ የዳታ ትንተና እና አሁን ያሉ ሁኔታዎች ላይ በሚካሄደው ጥናት ላይ ተመስርቶ የኮሪደሩን ሁኔታዎች የሚያሻሽሉ የዲዛይን አማራጮች ያዘጋጃል። በዲዛይን አማራጮቹ ላይ ግብረ መልስ የሚሰጥባቸው ተጨማሪ እድሎች የሚኖሩ ሲሆን እነዚህም የፕሮጀክቱ የመጨረሻ ዲዛይን መረጃ ይሰጣሉ። ፕሮጀክቱን በ2025 ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዷል።
ይህ ፕሮጀክት የከተማው የተሟሉ መንገዶች የአምስት ዓመት የስራ እቅድ አካል ነው። ከተማው የሁሉንም የመንገድ ተጠቃሚዎች የትራፊክ እንቅስቃሴ ደህንነት ለማሻሻል ስለሚያደርጋቸው ጥረቶች በተመለከተ ተጨማሪ የተሟሉ መንገዶች እና Vision Zero (የዜሮ ራዕይ) ፕሮግራም ድህረገጾችን ይጎብኙ። ስለ South Pickett Street ኮሪደር ማሻሻያዎች ፕሮጀክት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት alexandriava.gov/go/5106ን ይጎብኙ።

